የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሀረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

## OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| 21ኛ አመት ቁጥር 5<br>21 th Year No. 5 | | ሀረር የካቲት 22 ቀን 2008 ዓ.ም<br>HARAR, March 1, 2016 |
| ያንዱ ዋጋ ብር 2፡00<br>Unit Price Birr 2፡00 | በሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖ.ሣ.ቁ. 952<br>P.O.Box 952 |


ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 133/2008

በሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት በ2008 በጀት አመት ለልማታዊ ሴፍቲኔት ኘሮግራም ማስፈፀሚያና በተጨማሪ ለተደገፈ ካፒታል ኘሮጀክት ማስፈፀሚያ ከተካባጅ በጀት የታወጀ የተጨማሪ በጀት አዋጅ ........ ገጽ 1089


## አዋጅ ቁጥር 133/2008

## በሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት በ2008 በጀት አመት ለልማታዊ ሴፍቲኔት ኘሮግራም ማስፈፀሚያ በተጨማሪ ለተደገፈ ካፒታል ኘሮጀክት ማስፈፀሚያ ከተካባጅ በጀት የታወጀ ተጨማሪ በጀት አዋጅ

የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ ምክር ቤት በተሻሻለው የሀረሪ ህዝብ ክልል ህገ-መንግስት አንቀጽ 51 ንኡስ አንቀጽ 2(ነ) እና በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ 88/2002 አንቀጽ 27 ላይ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚከተለውን ተጨማሪ በጀት አውጇል ::

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ «የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት በ2008 በጀት አመት ለልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ በድጋሚ ለተላከውና የ11ኛውን የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች በዓል ዝግጅት ለሚካሄድበት ዘመናዊ ስታዲየም ግንባታ ከተካባጅ በጀት ላይ በካፒታል በጀት የታወጀ ተጨማሪ በጀት አዋጅ ቁጥር 133/2008 » ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ::

**2. ስለተጨማሪ ገቢና ምንጭ**

ሀ. ለልማታዊ ሴፍቲኔት ፐሮግራም ማስፈጸሚያ

ብር 15,230,201

ለ. ለዘመናዊ ስታዲየም ግንባታ ከተካባጅ በጀት ላይ ብር 150,000,000

ድምር ብር 165,230,201

ለልማታዊ ሴፍቲኔት ኘሮግራም ማስፈፀሚያ ከልማት አጋሮች በድጋሚ በተገኘ እርዳታ የክልላችን ድርሻ እና ለዘመናዊ ስታዲየም ግንባታ ከክልሉ ተካባጅ በጀት::

**3. ስለወጪ ምደባ**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ (2) ላይ የተመለከተው ተ ጨማሪ በጀት በሚከተሉት ዘርፎች ተደልድሎ የወጪ አመዳደብ ከዚህ በታች በተገለጸው አይነት ይሆናል::

ሀ. በካፒታል ወጪ ለልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ ከልማት አጋሮች በተገኘ ዕርዳታ የክልላችን ድርሻ በድጋሚ የተላከ ብር 15,230,201

ለ. ለዘመናዊ ስታዲየም ግንባታ ከተካባጅ በጅት ላይ ብር 150,000,000

**4. ክፍያ ስለመፈጸም**

ጉዳዩ የሚመለከተው የሴክተር መስሪያ ቤት የምግብ ዋስትና ጽህፈት ቤት ለልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም እንዲሁም የክልሉ ስፖርት ኮሚሽን ለዘመናዊ ስታዲየም ግንባታ ስራ ላይ እንዲያውል ታዟዋል::

**5. አዋጅ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከየካቲት 22 ቀን 2008 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ሀረር የካቲት 22 ቀን 2008 ዓ/ም

ሙራድ አብዱልሃዲ

የሀረሪ ህዝብ ክልል መንግስት

ፕሬዝዳንት